**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Friday 6 May 2005 (morning)
Vendredi 6 mai 2005 (matin)
Viernes 6 de mayo de 2005 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ):: መልስህ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት:: በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል:: በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም::*

**ድራማ**

1. ተከታዩን

(ሀ) ፀሀፊ ተውኔቶች ተውኔት በሚጽፉበት ጊዜ ትኩረታቸው በቃላትና በጽሁፉ ላይ ብቻ ሳይሆን የተውኔቱን ትርጉም በሚያጎለብቱ ሌሎች ሁኔታዎች ላይም ጭምር ነው:: ያጠናሃቸውን ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) በማንኛውም ድራማ ከእውነታው አለም ለየት ባለ መልኩ ሁኔታዎች በመድረክ ላይ ይቀርባሉ:: ይህም የድራማው ዐለም በተለምዶ የሚፈቀደው ነው:: ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ድራማዎች በመመርኮዝ ግለጽ::

**ረጅም ልቦለድ**

2. ተከታዩን

(ሀ) አንድ ልቦለድ አንባቢውን ለመማረክ ገፀባህሪያቱ ተአማኒ ሊሆኑ ይገባል:: ያጠናሃቸውን ሁለት ወይም ሶስት ስራዎች በመጥቀስ የዚህን ዐረፍተነገር ትክክለኛነት ግለጽ:: መልስህ ደራስያኑ ገፀባህርያቶቻቸውን ተአማኒ አድርገው ማቅረቡ የተሳካላቸውና ያልተሳካላቸው መሆኑን የሚያመለክት ይሁን::

ወይም ቀጣዩን ምረጥ::

(ለ) ደራስያን የልቦለዶቻቸውን ዋና ዋና ድርጊቶች የሚያቀርቡበት ቅደም ተከተል ልቦለዱ ለአንባቢው በሚሰጠው ትርጉምና በማራኪንቱ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ የልቦለዱ ዋና ዋና ድርጊቶች የቀረቡበትን ቅደም ተከተልና ድርጊቶቹ በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ስፍራ አስረዳ:: ከእያንዳንዱ ልቦለድ ቢያንስ አንድ ድርጊት በምሳሌነት በመጥቀስ መልስህን ስጥ::

**ስነግጥም**

3. ተከታዩን

(ሀ) ገጣምያን በአንባቢው አመለከከት ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የሚችሉት እንዴት ነው? ያጠናሃቸውን ግጥሞች ምሣሌ በማድረግ መልስህን ስጥ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) ገጣምያን ሃሳባቸውን በቃላት ለመግለጽ የተለያዩ ስልቶች ይጠቀማሉ የሚለውን ሀሳብ ያነበብካቸውን ግጥሞች በማወዳደር ገጣምያኑ የተጠቀሙባቸውን ስልቶችና የስልቶቹንም ጥቅም አብራራ።

**ስድንባብ**

4. ተከታዩን

(ሀ) የስድ ጽሁፍ(ለምሳሌም ወግ) ፀሀፊዎች በአንባቢው ላይ ማሳደር የሚፈልጉትን ተጽእኖ የሚያሳድሩት በሚያቀርቡት ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በሃሳብ አገላለፃቸውም ጭምር ነው። ይህንን አረፍተ ነገር ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በመመርኮዝ ግለጽ።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) ስድ ጽሁፎች (ለምሳሌም ወጎች) አመለካከቶችን የያዙ በመሆናቸው አንድን ጉዳይ ሳይሆን ጉዳዩን መመልከቻ መንገዶችን ያቀርባሉ። ይህንን አረፍተ ነገር መሰረት በማድረግ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች አወዳድር።

**አጭር ልቦለድ**

5. ተከታዩን

(ሀ) ቁጥብነት የአጭር ልቦለድ ዋነኛ መለያ ባህሪ ቢሆንም አንዳንድ ደራስያን ከሌሎች በበለጠ በቁጥብነት ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። ይህንን አረፍተ ነገር ያጠናሃቸውን ሁለት ደራስያን ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር ግለጽ። መልስህ ቢያንስ ሶስት ወይም አራት አጭር ልቦለዶች መሰረት ያደረገ ይሁን።

ወይም ቀጣዩን ምረጥ።

(ለ) የአንድን አጭር ልቦለድ ጭብጥ ለማወቅ አንዱ ዘዴ በልቦለዱ አላባውያን (ኤለመንትስ) ላይ ማተኮር ነው። ይህንን ሃሳብ ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ።

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**6.** ከሚከተሉት አንዱን መርጠህ መልስ(ሽ)::

(ሀ) ደራስያን ከሚፈልጉት ግብ ለመድረስ መቼትን እንዴትና ለምን ይጠቀሙበታል? ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ጥያቄውን መልስ::

ወይም

(ለ) ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ደራስያኑ አጋጣሚዎችንና ባህርያትን በአስቂኝ ሁኔታ ያቀረቡበትን መንገድ አብራራ:: አስቂኝ አቀራረባቸው ስራዎቹን ለመረዳት ያደረገውን አስተዋጽኦም ግለጽ::

ወይም

(ሐ) አብዛኛው ስነጽሁፍ የሰውን ልጆች ተፈጥሮ በመመርመር ያቀርባል:: ያጠናሃቸውን ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ደራስያን የተለያዩ ስነጽሁፋዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የሰውን ልጅ ተፈጥሮ እንዴት እንደሚያቀርቡ አስረዳ::

ወይም

(መ) ማንኛውም ጽሁፍ ዋነኛ አላማው አንባቢው አንድን ጉዳይ እንዲረዳና እንዲሰማው ማድረግ ነው ይባላል:: ያጠናሃቸውን ስራዎች ይዘትና የአፃፃፍ ስልት በመጥቀስ የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት አስረዳ::